የ2012 በጀት ዓመት
የፕሮግራም በጀት
አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ



ገንዘብ ሚኒስቴር

ጥር /2011

ማውጫ

1. መግቢያ 3
2. የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ለማዘጋጀት መወሰድ ያለባቸው ታሳቢዎች 4
   2.1. ነባር መ/ቤቶችን በተመለከተ፣ 4
   2.2. የተዋሃዱ ወይም የተለያዩ መ/ቤቶችን በተመለከተ፣ 5
   2.3. አዲስ የተቋቋሙ መ/ቤቶችን በተመለከተ፣ 6
   2.4. ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፡- 6
3. የፕሮግራም በጀት ዝርዝር አዘገጃጀትና አቀራረብ 7
   3.1 ደረጃ 1፡– የፕሮግራም በጀት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዕቀፍ 7
   3.2. ደረጃ 2፡– ውጤቶች፣ አመልካቾች፣ ግቦችና የሦስት ዓመት የወጪ ግምት 10
   3.3. ደረጃ 3፡– የዓመታዊ በጀት ዝግጅት 12
4. የፕሮግራም በጀት የወጪ ስሌት አሠራር 14
5. ሥርዓተ ፆታ 15
6. የ2012 የፕሮግራም በጀት የተጠቃለለ የበጀት ጥያቄ ሰነድ ይዘት/contents/ 16

1. መግቢያ

በየዓመቱ የሚመደበው በጀት የተፈለገውን ዓላማ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲመታ ከተፈለገ ወጪ የሚደረገው ሀብት ውጤታማ ሊያደርገው በሚችል ስርዓት መዘጋጀት እና ስርዓቱ በሚጠይቀው ስታንዳርድ መሰረት መተግበር ይጠበቅበታል። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ በፌዴራል ደረጃ የውጤት ሰንሰለት /Result Chain/ በመጠቀም ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት ያደረገውን የልማት እቅድን ከበጀት፤ በጀትን ከውጤት ጋር በሚያዛምድ የፕሮግራም በጀት አሠራር ሥርዓት ዓመታዊ በጀቱ እየተዘጋጀ ይገኛል።

የፕሮግራም በጀት አሠራር ሥርዓት ዋና ዓላማ የፕሮግራም አደረጃጀትን /Program Based/ እና የውጤታማነት መረጃን /Performance Information/ በመጠቀም ሀብትን ለውጤት መመደብ ነው። የውጤታማነት መረጃ /Performance Information/ የሚባሉት የፕሮግራም ዓላማ /Outcome/፣ የፕሮግራም ውጤት /Output/፣ የውጤት መለኪያ /Indicators/ እና ግብ /Target/ ናቸው። በኢትዮጵያ የፕሮግራም በጀት አሠራር በጀትን ከውጤት ጋር ለማዛመድና የስትራቴጂክ ግቦችን አፈፃፀም ለመለካት እንዲቻል የተቀረፀ በመሆኑና ተንከባላይ /rolling/ ስላልሆነ በየሦስት ዓመት በዙር /cycle/ መልክ የሚፈጸም ነው። በዚህም መሰረት የሶስተኛው ዙር የ2010-2012 የፕሮግራም በጀት ተዘጋጅቶ ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

የ2012 የፕሮግራም በጀት የዚሁ የሶስተኛው ዙር የ2010-2012 የፕሮግራም በጀት ዘመን አካል የመጨረሻ ዓመት መሆኑ ታውቆ የ2012 በጀት ዓመት የአንድ ዓመት የፕሮግራም በጀት ጥያቄ በዚህ የፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ መሠረት ተዘጋጅቶ እስከ መጋቢት 15 ቀን 2011 ድረስ መቅረብ ይኖርበታል።

2. የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ለማዘጋጀት መወሰድ ያለባቸው ታሳቢዎች

በኢትዮጵያ በፌዴራል ደረጃ እየተተገበረ በሚገኘው የፕሮግራም በጀት አሰራር መሰረት በአንድ ፕሮግራም ዘመን የተቀረጹ ፕሮግራሞች እና ዓላማዎች አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ለፕሮግራም ዘመኑ /ሶስት ዓመታት/ የማይቀየሩ በመሆናቸው ያለምንም ማሻሻያ ፕሮግራሞች አና ዓላማዎች መቀጠል እንደሚገባቸው ይገልጻል። በዚሁ መሰረት የ2012 የፕሮግራም በጀት የ2010-2012 የፕሮግራም በጀት ዘመን አካል በመሆኑ ለ2010-2012 ለሶስት ዓመታት የታቀዱ ፕሮግራሞችና ዓላማዎች ሳይቀየሩ ለ2012 በጀት ዓመት መቀጠል ይገባቸው ነበር። ሆኖም በ2010 እና በ2011 በተለይም በ2011 በጀት ዓመት መንግስት እንደገና ራሱን በማደራጀቱ ምክንያት የተለያዩ ተቋማት እንዲፈርሱ፣ እንዲዋሃዱና እንዲለያዩ ሆኗል።

በመሆኑም የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ሲዘጋጅ የሚቀጥሉትን ታሳቢዎች መሰረት ማድረግ ይገባል።

2.1. ነባር መ/ቤቶችን በተመለከተ፣

የ2010-2012 የሶስት ዓመት የፕሮግራም በጀት ከታቀደ በኃላ በመንግስት በኩል የመ/ቤቱ ስልጣንና ኃላፊነት ካልተሻሻለ የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት መ/ቤቱ ሲያዘጋጅ፡-

- ለ2010-2012 የተቀመጡ ዓላማዎችንና ፕሮግራሞችን በቀጥታ በመውሰድ /በ2010 በጀት ዓመት ተቋቁሞ የነበረ ከሆነ ለሁለት ዓመት /ለ2011-2012/ የታቀዱ ፕሮግራሞችና ዓላማዎች በቀጥታ በመውሰድ/፣
- ለ2010-2012 የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት በ2012 የተቀረጹ ውጤቶች አና የውጤት አመልካቾች አና ግቦች የሚቀጥሉ ከሆነ እንዲቀጥሉ በማድረግ፣ መሻሻል ካለባቸው በማሻሻል እንዲሁም አዲስ መጨመር ያለባቸው ውጤቶች ካሉ በማካተት በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ የውጤቶች አፈጻጸም የሚደረስበትን እንደ መነሻ /baseline/ በመውሰድ ለ2012 የሚያገለግሉ የ2012 ውጤቶች /Output/ እና የውጤቶች አመልካቾች እና ግቦች ማዘጋጀት ይገባል።

- በተጨማሪም የተቀረጹትን ውጤቶች ለማሳካት በ2012 በጀት ዓመት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችና የመደበኛ ዋና ተግባራቶችን በመቅረጽ የፕሮግራም በጀቱ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል::

2.2. የተዋሃዱ ወይም የተለያዩ መ/ቤቶችን በተመለከተ፣

የ2010-2012 የሶስት ዓመት የፕሮግራም በጀት ከታቀደ በኃላ በመንግስት በኩል ከሌላ መ/ቤት ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲለያይ በመደረጉ ምክንያት የመ/ቤቱ ስልጣንና ኃላፊነት ከተሻሻለ መ/ቤቱ የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ሲያዘጋጅ፡-

- ለነባር ፕሮግራሞች
  - ለ2010-2012 የተቀመጡ ዓላማዎችንና ፕሮግራሞችን በቀጥታ በመውሰድ /በ2010 በጀት ዓመት ተቋቁሞ የነበረ ከሆነ ለሁለት ዓመት /ለ2011-2012/ የታቀዱ ፕሮግራሞችና ዓላማዎች በቀጥታ በመውሰድ/፣
  - ለ2010-2012 የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት በ2012 የተቀረጹ ውጤቶች እና የውጤት አመልካቾች እና ግቦች የሚቀጥሉ ከሆነ እንዲቀጥሉ በማድረግ፣ መሻሻል ካለባቸው በማሻሻል እንዲሁም አዲስ መጨመር ያለባቸው ውጤቶች ካሉ በማካተት በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ የውጤቶች አፈጻጸም የሚደረስበትን እንደ መነሻ /baseline/ በመውሰድ ለ2012 የሚያገለግሉ የ2012 ውጤቶች /Output/ እና የውጤቶች አመልካቾች እና ግቦች ማዘጋጀት ይገባል::
- ለአዲስ ፕሮግራሞች
  - በውህደቱ /በመለያየቱ ምክንያት ፕሮግራሞች ተዋህደው /ተለያይተው አዲስ ፕሮግራም ከተፈጠረ ለተፈጠረው ፕሮግራም የ2012 የአንድ ዓመት የሚሆን መነሻና መድረሻ ያለው ዓላማ ሊቀረጽ ይገባል፣
  - ለ2012 የተቀረጹ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ ውጤቶችን በመቅረጽ እና ለእነዚህም ውጤቶች መነሻ /baseline/ በማስቀመጥ ለአንድ ዓመት የሚያገለግሉ የ2012 ውጤቶች /Output/ እና የውጤቶች አመልካቾች እና ግቦች ማዘጋጀት ይገባል::

- በተጨማሪም የተቀረጹትን ውጤቶች ለማሳካት በ2012 በጀት ዓመት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችና የመደበኛ ዋና ተግባራትን በመቅረጽ የፕሮግራም በጀቱ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል።

2.3. አዲስ የተቋቋሙ መ/ቤቶችን በተመለከተ፣

የ2011 በጀት ዓመት ከጸደቀ በኃላ የተቋቋመ መ/ቤት ከሆነ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ መ/ቤቱ የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ሲያዘጋጅ፡-

- ለ2012 በጀት ዓመት የሚሆኑ መነሻ እና መድረሻ ያላቸው የአንድ ዓመት ዓላማዎች /Outcomes/ እና ፕሮግራሞች በመቅረጽ፣
- ለ2012 የተቀረጹ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ ውጤቶችን በመቅረጽ እና ለእነዚህም ውጤቶች መነሻ /baseline/ በማስቀመጥ ለአንድ ዓመት የሚያገለግሉ የ2012 ውጤቶች /Output/ እና የውጤቶች አመልካቾች እና ግቦች በማዘጋጀት፣
- በተጨማሪም የተቀረጹትን ውጤቶች ለማሳካት በ2012 በጀት ዓመት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችና የመደበኛ ዋና ተግባራትን በመቅረጽ የፕሮግራም በጀቱ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል።

2.4. ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፡-

- ነባር ፕሮጀክቶች ያሉበትን ደረጃ በማወቅ አስፈላጊውን ፋይናንስ መመደብ እንዲቻል የፕሮጀክቶች ሙሉ መግለጫ /Project Profile/ ከዚህ የአዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ቅጽ መሰረት ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል። በጥቅል የተፈቀዱ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ስራዎች /Components/ በአግባቡ ተገልጸው መቅረብ ይገባቸዋል።
- አዲስ ፕሮጀክቶች ለ2012 የበጀት ጥያቄ ከቀረቡ የተሟላ የፕሮጀክት የጥናት ሰነድ ከበጀት ጥያቄው ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።
- ለነባር ፕሮጀክቶች በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት የፕሮጀክቶች ሙሉ መግለጫ /Project Profile/ ወይም ለአዲስ ፕሮጀክት የፕሮጀክቱ ሰነድ የማይቀርብ ከሆነ ለፕሮጀክቶች ለ2012 በጀት የማይመደብ ይሆናል።

- በዩኒቨርሲቲዎች የሚካሄዱ የነባር ፕሮጀክቶች ማጠናቀቂያን በተመለከተ፡- በ2005 ከተላለፈው የፕሮጀክት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ ውጪ በዩኒቨርሲቲዎች በነባር ፕሮጀክቶች ስም በየዓመቱ አዳዲስ ፕሮጀክቶች እየተካሄዱ የሚገኙ በመሆኑ በ2012 በጀት ዓመት ለነባር ፕሮጀክቶች ማጠናቀቂያ ተብሎ በጀት ስለማይመደብ በነባር ፕሮጀክት ስም ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ካሉ በፕሮጀክት ደረጃ ተለይተው መቅረብ አለባቸው።

3. የፕሮግራም በጀት ዝርዝር አዘገጃጀትና አቀራረብ

የፕሮግራም በጀት ዝግጅት የመ/ቤቱን ዓላማዎች በግብ ስኬት ደረጃ /Outcome/ እና ፕሮግራሞች መቅረጽ፣ ውጤቶችን /Output/ እና ለውጤቶች አመልካቾች እና ግቦች ማስቀመጥ እንዲሁም ውጤቶችን ለማሳካት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች እና ዋና ተግባራት ማስቀመጥን ያካትታል። የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ሦስት ደረጃዎች ይኖሩታል። እነሱም፡-

ደረጃ 1፡- የፕሮግራም በጀት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዕቀፍ

ደረጃ 2፡ ውጤቶች፣ አመልካቾች፣ ግቦችና የመካከለኛ ዘመን የወጪ ግምት

ደረጃ 3፡- የዓመታዊ በጀት ዝግጅት ናቸው።

3.1 ደረጃ 1፡- የፕሮግራም በጀት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዕቀፍ

የፕሮግራም በጀት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዕቀፍ የሶስት ዓመት የመሠረተ ልማት እና አገልግሎት አሰጣጥ ዕይታዎችን፣ ስትራቴጂክ (SMART) ዓላማዎችንና ፕሮግራሞችን የመቅረጽ ተግባራትን የሚያካትት ነው። በዚህ መሠረት የፕሮግራም በጀት ስትራቴጂክ ማዕቀፍ የሚከተሉትን ያካትታል።

- የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ
- የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሴክተር ዕቅድ /መ/ቤቱን የሚመለከት/
- የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ /የመ/ቤቱ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ጣሪያ/
- የስትራቴጂክ ዓላማዎችንና ፕሮግራሞች መቅረጽ (የፕሮግራሞችን መግለጫ ጨምሮ)
- የስትራቴጂክ ዓላማዎች ቅደም ተከተል ማውጣት

በደረጃ አንድ የፕሮግራም በጀት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዕቀፍ ውስጥ የሚጠቃለሉ ዋና ዋና ክፍሎች ዋነኛው ለሶስት ዓመታት የሚያገለግሉ ዓላማዎችንና ፕሮግራሞችን

መቅረጽ ነው:: ዓላማዎች አንድ መ/ቤት በሶስት ዓመታት ሊደርስባቸው የሚችሉ መነሻ እና መድረሻ ያላቸው ሆነው በግብ ስኬት /Outcome/ ደረጃ መቀረጽ ይገባቸዋል:: ይህ ተግባር በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የ2010-2012 የሶስት ዓመት የፕሮግራም በጀት በሚዘጋጀበት ወቅት መከናወኑ ይታወቃል:: ሆኖም የ2010-2012 የሶስት ዓመት የፕሮግራም በጀት ከተዘጋጀ በኃላ መ/ቤቶች የተለያዩ፣ የተዋሃዱ እና እንደ አዲስ የተቋቋሙ በመሆናቸው የ2012 የፕሮግራም በጀት ጥያቄ ሲዘጋጅ ከላይ በክፍል 2 የተገለጸውን እና የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ ማዘጋጀት ይገባል::

- **ስትራቴጂክ SMART ዓላማዎችና ፕሮግራሞች መቅረጽ**

የመጀመሪያው ዙር የፕሮግራም በጀት ዘመን /2004-2006/ በ2006 በጀት ዓመት፣ የሁለተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት ዘመን /የ2007-2009/ በ2009 በጀት ዓመት ተጠናቆ የሶስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት ዘመን /የ2010-2012/ ለ2007-2009 የተቀመጡ ዓላማዎችንና ፕሮግራሞችን በመገምገም እና በ2009 የተደረሰበትን የግብ ስኬት/Outcome/ አፈጻጸም እንደ መነሻ /baseline/ በመውሰድ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መዘጋጀቱ ይታወቃል:: በዚህ መሰረት ከላይ በክፍል 2 በተገለጸው መሰረት ነባር መ/ቤቶች በ2009 በጀት ዓመተ መጨረሻ የተቀረጹትን ፕሮግራሞች እና ዓላማዎች በመጠቀም የ2012 የፕሮግራም በጀት ማዘጋጀት የሚችሉ ሲሆን የ2010-2012 የሶስት ዓመት ወይም የ2011-2012 የሁለት ዓመት የፕሮግራም በጀት ያልታቀደላቸው ግን ለ2012 የሚያገለግሉ ፕሮግራሞች እና ዓላማዎችን መቅረጽ ይገባቸዋል::

አዲስ መ/ቤቶች ወይም በመለያየታቸውና በመዋሃዳቸው ምክንያት አዲስ ፕሮግራሞችን መቅረጽ ለሚያስፈልጋቸው መ/ቤቶች ለ2012 በጀት ዓመት የአንድ ዓመት የሚሆኑ ዓላማዎችንና ፕሮግራሞች ለመቅረጽ የሚከተሉትን ነጥቦች መነሻ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል::

- ዓላማዎች የተለዩ፣ የሚለኩ፣ የሚደረስባቸው፣ አግባብነት ያላቸው፣ የጊዜ ወሰን ያላቸው /SMART/ መሆን አለባቸው:: ዓላማ /outcome/ የሚባለው አንድ ሊደረስበት የተፈለገ የመጨረሻ ውጤት ነው:: ዓላማዎች በግብ ስኬት /outcome/ ደረጃ የሚገለጹ እና መነሻን /baseline/ መሰረት ተደርገው የሚቀረጹ ናቸው::
- የስትራቴጂክ ዓላማዎችን ለመወሰን መነሻ የሚሆኑት:-
  - የመ/ቤቱ ተልዕኮና ማንዴት

- የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ
- የመ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ
- ሊደረስባቸው የሚችሉ ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃዎች ናቸው::

- ስትራቴጂክ ዓላማዎች ከተለዩ በኋላ እነዚህን ዓላማዎች የሚገልጹ ፕሮግራሞች/ንኡስ ፕሮግራሞች ይመሠረታሉ:: ይሁንና ንኡስ ፕሮግራሞች የሚመሠረቱት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው::

- ፕሮግራም ማለት የመስሪያ ቤቱን ዓላማ ለማስፈጸምና ስትራቴጂክ ግቦችን ለማስገኘት በአንድ የፕሮግራም ሥራ አመራር /Program Management /ሥር ወጪ የሚመደብላቸውን ውጤቶች፣ የመደበኛ ዋና ተግባራትን እና የካፒታል ፕሮጀክቶችን በማሰባሰብ የሚይዝ ነው::

- ንዑስ ፕሮግራም ማለት ፤ ከዋናው ፕሮግራም አንፃር የሚዛመዱ ነገር ግን በፕሮግራሙ ስር የተለየ ዓላማ ያላቸው እና ተለይተው የሚገለጹ አካላት /Components/ ካሉ በንዑስ ፕሮግራም ደረጃ ሊዋቀር ይችላል::

- ለእያንዳንዱ ፕሮግራም/ንኡስ ፕሮግራም ስለፕሮግራሙ ይዘት አጭር መግለጫ መቅረብ ይኖርበታል::

- የፕሮግራም/ንኡስ ፕሮግራም ኃላፊ የግለሰብ ስም ሳይሆን በመ/ቤቱ መዋቅር መሠረት ኃላፊ የሚሆነው ዳይሬክቶሬት፣ መምሪያ፣ ወዘተ መጻፍ አለበት::

- ዓላማዎች ከተለዩ በኋላ በቅደም ተከተል መቀመጥ ይኖርባቸዋል:: ይህም የሚደረግበት ምክንያት በአቅም ውሱንነት ሁሉንም ዓላማዎች በአንድ ጊዜ ለማሳካት የማይቻል ሆኖ ከተገኘ በቅደም ተከተል ለማስፈጸም ነው:: የዓላማዎችን ቅደም ተከተል ለማውጣት በ2007 የፕሮግራም በጀት ማንዋል ገጽ 22 የተመለከቱትን መመዘኛዎች (criteria) እንደአግባብነቱ መጠቀም ይቻላል::
- የሥራ አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት በፕሮግራሞች ቅደም ተከተል የመጀመሪያ ተራ ቁጥር ይሰጠዋል::

3.2. ደረጃ 2:– ውጤቶች፣ አመልካቾች፣ ግቦችና የሦስት ዓመት የወጪ ግምት:-

ደረጃ ሁለት የውጤታማነት መረጃ /Performance Information/ አካል የሆኑት ውጤቶች /Outputs/፣ የውጤቶች መለኪያዎች እና ግቦች የሚቀርብበት ሲሆን በደረጃ 1 የተቀረጹትን ዓላማዎች መሳካታቸውን ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ ናቸው። ውጤቶች /Outputs/፣ የውጤቶች መለኪያዎች እና ግቦች ለሶስት ዓመት የታቀደውን ዓላማ በየዓመቱ ስለመሳካቱ የሚገልጹ ቢሆኑም የባለፉት ዓመታት የፕሮግራም በጀት ዝግጅት እና አፈጻጸም ሲታይ በአብዛኛው በመ/ቤቶች በኩል እየተቀረጹ ያሉ ውጤቶች፣ የውጤት አመልካቾች እና ግቦች ደረጃቸውን ያልጠበቁ በመሆናቸው የመ/ቤቶችን እቅድ እና አፈጻጸም ለመገመገም አስቸግሯል። በመሆኑም የ2012 በጀት ዓመት የአንድ ዓመት የፕሮግራም በጀት ጥያቄ ሲዘጋጅ ለውጤቶች፣ ለውጤት አመልካቾች እና ለግቦች ልዩ ትኩረት በመስጠት ሊሆን ይገባል።

የፕሮግራም/ንዑስ ፕሮግራሞች ውጤቶች፣ የውጤት የአፈጻጸም አመልካቾች/መለኪያዎች /Performance Indicators /Measures// እና ግቦች /Targets/ ከላይ እንደተገለጸው ዓላማዎችን ሊያስፈጽሙ እና መ/ቤቱ በየዓመቱ ሊገመገምበት ወይም ሊለካበት የሚችሉ መሆን አለባቸው። በዚሁ መሰረት በክፍል ሁለት/2/ በተቀመጡት ታሳቢዎች መሰረት እያንዳንድ መ/ቤት ያስቀመጣቸውን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ ለ2012 በጀት ዓመት የሚያገለግሉ ውጤቶችን በባለፈው ዓመት ከተቀረጸው በመውሰድ፣ በማሻሻል ወይም በመቅረጽ ማዘጋጀት ይገባዋል።

በደረጃ ሁለት ውጤቶች በአግባቡ ከተቀረጹ በኋላ የእያንዳንዱ ውጤት የአፈጻጸም አመልካቾች/መለኪያዎች /Performance Indicators /Measures/ እና ግቦች /Targets/ ተለይተው መታወቅ ይኖርባቸዋል። በመጨረሻም ለእያንዳንዱ ውጤት የአፈጻጸም አመልካቾችንና ግቦችን መሰረት በማድረግ የእያንዳንዱ ዓመት የወጪ ግምት የወጪ አሸፋፈን በፋይናንስ ምንጭ መሰላት ይኖርበታል። የወጪ ግምቱ በተሰጠው ጣሪያ መሠረት ለአንድ ዓመት ከላይ ወደ ታች በቅጽ አበማ1 /የ2012 ዓመት የፕሮግራም በጀት ውጤት /Output/ ማጠቃለያ/ የሚዘጋጅ ሲሆን የውጤቶች ወጪ ተገምቶ የየፕሮግራሙ የወጪ ፍላጐት አካል ይሆናል።

I. ውጤት/output/ ማለት ማናቸውም ተግባራት ተከናውነው የሚገኙ እና ለንብረተሰቡ የሚሰጡ አገልግሎቶችና ምርቶች ናቸው:: ውጤቶች በየጊዜው የመ/ቤቱ አፈፃፀም ከመ/ቤቱ ተልኮና ማንዴት አንጻር መ/ቤቱ ራሱን እንዲሁም በውጭ አካላት የሚለካበትና የሚገመገምበት ስለሆነ ትኩረት ተሰጥቶት ለፕሮግራሙ ዓላማ መሳካት ተገቢና ዋነኛ ውጤቶች /Main Output/ የሆኑት ተለይተው ሊቀረጹ ይገባል::

ውጤቶች:-

- ከመ/ቤቱ ውጭ ለግለሰብም ሆነ ድርጅቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችና ምርቶች መሆን አለባቸው፣
- ተለይተው የሚታወቁና የሚለኩ መሆን አለባቸው፣
- በተግባር መልክ መገለጽ የለባቸውም፣
- በመሃል ላይ የሚገኙ ውጤቶች /intermediate output/ ሳይሆኑ የመጨረሻ ውጤቶች መሆን አለባቸው፣
- ዓላማና ፕሮግራሙን ሊያሳኩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፣
- ከመደበኛ ተግባራት እና/ወይም ከካፒታል ፕሮጀክቶች ስብስብ ይመነጫሉ፣

በሌላ በኩል በሥራ አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ሥር ያሉ የልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች አገልግሎቶች በመ/ቤቱ ውስጥ ላሉት ዓላማ አስፈጻሚ ፕሮግራሞች የውስጥ የድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆኑ ውጤታቸው ተለይቶ የሚታይ ሳይሆን በሌሎቹ ዓላማ አስፈጻሚ ፕሮግራሞች ላይ የሚንፀባረቅ ነው:: በመሆኑም በዚህ ፕሮግራም ሥር ያሉ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች በፕሮግራሙ ሥር ተጠቃለው "የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች" ተብለው እንደ አንድ ውጤት ይቀመጣሉ:: ከዚህም ሌላ በሥራ አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ሥር ያሉ የሥራ ክፍሎች በንዑስ ፕሮግራም ደረጃ መዘርዘር የለባቸውም:: ሆኖም በሌሎች ዓላማ አስፈጻሚ ፕሮግራሞች ተለይተው ሊቀመጡ የማይችሉ የካፒታል ፕሮጀክቶች በዚህ ፕሮግራም ሥር ሊቀመጡ ይችላሉ::



II. የአፈጻጸም አመልካቾች/መለኪያዎች

የአፈጻጸም አመልካቾች/መለኪያዎች የሚባሉት የአሃዝ መለኪያዎች (Quantitative Measures) ሆነው ስለ ፕሮግራሞች ውጤታማነት /Effectiveness/ እና የወጪ ቆጣቢነትን /Efficiency/ መረጃ የሚሰጡ ናቸው። ስለሆነም ውጤቶች ከተዘረዘሩ በኋላ ለእያንዳንዱ ውጤት የውጤት የአፈጻጸም አመልካቾች መቀመጥ የሚኖርበት ሲሆን የሚቀመጠውም የውጤት የአፈጻጸም አመልካች እያንዳንዱን ውጤት መለካትና በኋላም በክትትልና ግምገማ ወቅት ውጤቱ መሳካቱን ሊያሳይ በሚችል መልኩ መሆን ይገባዋል። ለአንድ ውጤት ከአራቱ የውጤት አመልካቾች /የመጠን፣ የጥራት፣ የወጪ ቆጣቢነት እና የፍሀታዊነት/ መካከል እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ አመልካች መጠቀም ይገባል።

III. ግብ /target/

ግብ /target/ ማለት መ/ቤቱ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሊያሳካ ያቀደው የየፕሮግራሞቹ ውጤቶች የአፈጻጸም ደረጃ ነው። ግቦች ለእያንዳንዱ ውጤት በአፈጻጸም አመልካቾች ትይዩ መሰረት ይቀመጣሉ። የሚታቀዱ ግቦችን ለማስቀመጥ በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ ሊደረስበት የሚችል የውጤት /Output/ የግቦች አፈጻጸም /baseline/ መሰረት በማድረግ የ2012 በጀት ዓመት የአንድ ዓመት የውጤት ግቦች ሊቀመጡ ይገባል።

3.3. ደረጃ 3፡– የዓመታዊ በጀት ዝግጅት

በደረጃ 3 የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ከላይ በደረጃ አንድ ለተቀረጹ ዓላማዎች እና በደረጃ ሁለት ለተቀረጹ ውጤቶች መሳካት የሚያገለግሉ በ2012 በጀት ዓመት መተግበር ያለባቸው ፕሮጀክቶችና እና የመደበኛ ዋና ተግባራት በመለየት በዝርዝር የወጪ መደቦችና በፋይናንስ ምንጭ በዓመታዊ በጀት ማቅረቢያ ቅጽ /ቅጽ አበማ2 - የ2012 የፕሮግራም በጀት መጠየቂያ - በፕሮጀክት፣ በዋና ዋና ተግባርና በዝርዝር የወጪ መደቦች/ በExcel የሚዘጋጅበት ነው።

የካፒታል ፕሮጀክቶች፡- የካፒታል ወጪ የሚመደብላቸውና የፕሮጀክትን ጽንሰ ሀሳብን የሚያሟላ መሆን ይገባዋል። ስለሆነም የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ቅጹ ላይ በተቀመጠው መሰረት የእያንዳንዱ የካፒታል ፕሮጀክቶች መግለጫ (Project Profile) በዓመታዊ በጀት

II. የአፈጻጸም አመልካቾች/መለኪያዎች

የአፈጻጸም አመልካቾች/መለኪያዎች የሚባሉት የአሃዝ መለኪያዎች (Quantitative Measures) ሆነው ስለ ፕሮግራሞች ውጤታማነት /Effectiveness/ እና የወጪ ቆጣቢነትን /Efficiency/ መረጃ የሚሰጡ ናቸው። ስለሆነም ውጤቶች ከተዘረዘሩ በኋላ ለእያንዳንዱ ውጤት የውጤት የአፈጻጸም አመልካቾች መቀመጥ የሚኖርበት ሲሆን የሚቀመጠውም የውጤት የአፈጻጸም አመልካች እያንዳንዱን ውጤት መለካትና በኋላም በክትትልና ግምገማ ወቅት ውጤቱ መሳካቱን ሊያሳይ በሚችል መልኩ መሆን ይገባዋል። ለአንድ ውጤት ከአራቱ የውጤት አመልካቾች /የመጠን፣ የጥራት፣ የወጪ ቆጣቢነት እና የፍሀታዊነት/ መካከል እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ አመልካች መጠቀም ይገባል።

III. ግብ /target/

ግብ /target/ ማለት መ/ቤቱ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሊያሳካ ያቀደው የየፕሮግራሞቹ ውጤቶች የአፈጻጸም ደረጃ ነው። ግቦች ለእያንዳንዱ ውጤት በአፈጻጸም አመልካቾች ትይዩ መሰረት ይቀመጣሉ። የሚታቀዱ ግቦችን ለማስቀመጥ በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ ሊደረስበት የሚችል የውጤት /Output/ የግቦች አፈጻጸም /baseline/ መሰረት በማድረግ የ2012 በጀት ዓመት የአንድ ዓመት የውጤት ግቦች ሊቀመጡ ይገባል።

3.3. ደረጃ 3:– የዓመታዊ በጀት ዝግጅት

በደረጃ 3 የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ከላይ በደረጃ አንድ ለተቀረጹ ዓላማዎች እና በደረጃ ሁለት ለተቀረጹ ውጤቶች መሳካት የሚያገለግሉ በ2012 በጀት ዓመት መተግበር ያለባቸው ፕሮጀክቶችና እና የመደበኛ ዋና ተግባራት በመለየት በዝርዝር የወጪ መደቦችና በፋይናንስ ምንጭ በዓመታዊ በጀት ማቅረቢያ ቅጽ /ቅጽ አበማ2 - የ2012 የፕሮግራም በጀት መጠየቂያ - በፕሮጀክት፣ በዋና ዋና ተግባርና በዝርዝር የወጪ መደቦች/ በExcel የሚዘጋጅበት ነው።

የካፒታል ፕሮጀክቶች፡- የካፒታል ወጪ የሚመደብላቸውና የፕሮጀክትን ጽንሰ ሀሳብን የሚያሟላ መሆን ይገባዋል። ስለሆነም የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ቅጹ ላይ በተቀመጠው መሰረት የእያንዳንዱ የካፒታል ፕሮጀክቶች መግለጫ (Project Profile) በዓመታዊ በጀት

ማቅረቢያ - በቅጽ አበማ3 እና ኮምፖኔንት ላላቸው ፕሮጀክቶች ደግሞ በተጨማሪነት የ2012 በጀት ዓመት የፕሮጀክት ኮምፖኔንቶች ዝርዝርና መግለጫ ማቅረቢያ ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል::

የመደበኛ ዋና ዋና ተግባራት /Main Activities/:- በመደበኛ ወጪ የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ፣ የፕሮግራሙን ውጤት ሊያስፈጽሙ የሚችሉ የዝርዝር ተግባራት ድምር ሆነው በጀት በወጪ ማዕከል ደረጃ ሊያዝላቸው እና በሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት /Chart of Account/ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ መሆን አለባቸው:: በመሆኑም መ/ቤቶች የመደበኛ ወጪአቸውን ሲያቀርቡ በዋና ተግባራት ደረጃ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን፣ ዝርዝር ተግባራትን እና የሥራ ሂደት ዝርዝርን /Process/ ማቅረብ የለባቸውም:: ለምሳሌ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራቶች፤

- ምርምርና ጥናቶችን መምረጥ
- የተመረጡ ምርምርና ጥናቶችን ማካሄድ
- ያለቁ የምርምር ሥራዎች ለህትመት ማብቃት
- የተመራማሪ ጥቅማ ጥቅም ማካሄድ
- የተመራማሪ የክሎት ማሻሻያ ስልጠና መስጠት

በዋና ተግባር ደረጃ ሲቀርቡ <u>ጥናትና ምርምር ማካሄድ</u> በሚል በአንድ ዋና ተግባር ይጠቃለላሉ::

- ✓ የ2011 በጀት ዓመት በጀት ሲዘጋጅ የተቀረጹ የመደበኛ ዋና ተግባራት ማሻሻያ ካላስፈለጋቸው በስተቀር የ2012 የፕሮግራም በጀት ጥያቄ በሚዘጋጅበት ጊዜ መቀየር የለባቸውም::
- ✓ ለተዋሃዱ ፕሮግራሞች ወይም አዲስ ለተፈጠሩ ፕሮግራሞች ከላይ በክፍል ሁለት በተገለጸው መሰረት ተግባራቶችን መቅረጽ ይገባል::

በስራ አመራርና አስተዳደር ስር የሚገኙ ዝርዝር ተግባራቶች ወይም የስራ ክፍሎች በአንድ ዋና ተግባር ድጋፍና አገልግሎት መስጠት በሚል ተጠቃለው መቅረብ ይኖርባቸዋል::

- ✓ በአንድ ፕሮግራም ሥር ያሉ ሰራተኞች ለተለያዩ ውጤቶችና ተግባራት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ከሆነ የደመወዝ በጀታቸው ተጠቃሎ በሚመለከተው ፕሮግራም በአንድ ውጤት ሥር በአንድ ተግባር ላይ ብቻ የሚያዝ ሲሆን፣

የአንድ የሥራ ክፍል/ዳይሬክቶሬት የሰራተኞች ደመወዝ በተለያዩ ውጤቶችና ተግባራት ተበታትኖ መያዝ የለበትም::

ዝርዝር የወጪ መደቦች፡- እየተሰራባቸው ያሉት የወጪ መደቦች በሂሳብ አወቃቀር ስርዓት በ6100፣ 6200፣ 6300፣ 6400 ሥር ያሉት *ዝርዝር የወጪ መደቦች* ናቸው:: ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ወይም ዋና ተግባር ወጪዎች በዝርዝር የወጪ መደቦች በቅጽ አበማ2 ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት::

- ✓ በደረጃ 3 ከታች ወደ ላይ የሚዘጋጀው ዓመታዊ በጀት /ቅጽ አበማ2/ በደረጃ 2 በፕሮግራምና በውጤት ደረጃ ከተዘጋጀው /ቅጽ አበማ1 / ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት::

4. የፕሮግራም በጀት የወጪ ስሌት አሠራር

የፕሮግራም በጀት ሲዘጋጅ በተገቢው መልኩ ሀብትን ከውጤት ጋር ለማቀናጀት ወጪዎችን መለየት ያስፈልጋል::

4.1 ቀጥተኛ ወጪዎች

ቀጥተኛ ወጪዎች ማለት በታቀደው መሠረት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ወጪዎች ናቸው:: ቀጥተኛ ወጪዎች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በቀጥታ የተሰማሩትን የሠራተኛ ወጪዎች ያጠቃልላል:: ይህም ደመወዝን፣ ምንዳን፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጥቅማጥቅሞች እና የአሰሪዎች የጡረታ መዋጮ ወጪዎችን ይሸፍናል:: በተጨማሪም ቀጥተኛ ወጪዎች ሰብዓዊ ያልሆኑ ወጪዎችን ይጨምራሉ:: ስለሆነም የየፕሮግራሞች ቀጥተኛ ወጪዎች ደመወዝን ጨምሮ በየፕሮግራሞቹ ተለይተው ይያዛሉ::

ከላይ እንደተገለጸው ቀጥተኛ የሆኑ ወጪዎች ደመወዝን ጨምሮ በየፕሮግራሞቹ መያዝ ያለበት ሲሆን የሌሎች ፕሮግራሞችን ደመወዝ በማጠቃለል በስራ አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ስር መቅረብ የለበትም::

4.2 ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች

በተቋም ውስጥ ደጋፊ ተግባራት (Staff functions) የሚባሉት ዋና ተግባራት (Line functions) ለሚሰጡት አገልግሎት ድጋፍ የሚሰጥ ነው:: በተጨማሪም ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች እያንዳንዱ የሥራ ክፍል በጋራ ከሚጠቀሙበት አገልግሎት ጋር የተያያዘ ነው::

ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች የአንድን መ/ቤት የዕቅድ፣ የፋይናንስ፣ የሰው ሀብት እና አዲት ዳይሬክቶሬቶች/መምሪያዎችን ወዘተ ያጠቃልላል:: ሌሎች የጋራ አገልግሎቶች የሚባሉት ደግሞ የጋራ አገልግሎት የሚሰጡ ሕንፃዎች የሕትመት ክፍሎች፣ የምዝገባ፣ የጋራ ጽዳት አገልግሎት፣ የጋራ ትራንስፖርት አቅራቢ ክፍል እና የመሳሰሉትን ያጠ ቃልላል::

በመሆኑም ለ2012 የፕሮግራም በጀት ዘመን ባለበጀት መ/ቤቶች *እነዚህን ወጪዎች በሥራ አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ሥር በማጠቃለል መያዝ ይኖርባቸዋል::*

4.3. የወጪ ስሌት:-

ለ2012 የፕሮግራም በጀት ዝግጅት የወጪ ስሌት ለመሥራት የሚከተሉትን ነጥቦች መነሻ ማድረግ ያስፈልጋል::

- ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ በመንግሥት የተወሰኑ ተመኖች እና ለቋሚ ዕቃዎች የተቀመጡ ስታንዳርዶች፣
- በመ/ቤቱ ወይም በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በማዕከል በቅርቡ የተደረጉ ግዥዎች የጨረታ ዋጋ እና የየካቲት ወር 2011 ዓ.ም የገበያ ዋጋ፣

5. *ሥርዓተ ፆታ*

የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ መንግስት በወሰደው ቁርጠኝነት መሰረት በሕገ መንግስቱ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን፣ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ፣ በመንግስት የጸደቁ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶችና ድንጋጌዎችን እንዲሁም በተለያዩ የሴክተር መ/ቤቶች ሥርዓተ ፆታን አካተው የወጡ ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በዕቅድና በበጀት ውስጥ ተካቶ መሰራት አለበት። ስለዚህም የፕሮግራም/ንዑስ ፕሮግራሞች ውጤቶች መለኪያዎች/አመልካቾች እና ግቦች /Targets/ በሚቀረጹበት ወቅት የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ የሚመለከት የፍታሀዊነት መለኪያ/አመልካች እና ግቦች /Targets/ አብሮ መካተት ይኖርበታል::

6. የ2012 የፕሮግራም በጀት የተጠቃለለ የበጀት ጥያቄ ሰነድ ይዘት/contents/

ከዚህ በላይ በቀረበው የፕሮግራም በጀት አዘገጃጀት መሠረት የሚዘጋጀው የአንድ ባለበጀት መ/ቤት የተጠቃለለ የበጀት ጥያቄ ሰነድ ይዘት የሚከተለው ይሆናል። አቀራረቡም በዚሁ ቅደም ተከተል መሰረት መሆን አለበት።

1. **መግቢያ**

መ/ቤቱ ስለ በጀቱ ይዘትና አጠቃላይ ጉዳዮች የሚገልጽበት፣

2. **የ2012 የፕሮግራም በጀት ማጠቃለያ**

ለበጀት ዓመቱ የተጠየቀው በጀት በጥቅል የሚገለጽበትና የተጠየቀው በጀት በመ/ቤቱ ከሚከተሉት መሰረታዊ ነጥቦች አንጻር ተገቢው ትንታኔ በአጭሩ የሚቀርብበት ነው።

- የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለመፈጸም የተጠየቀው በጀት የሚያደርገው አስተዋጽኦ፣
- የመደበኛና የካፒታል ወጪ ማጠቃለያ፣ የበጀት ጥያቄው ከተሰጠው ጣሪያ ጋር ያለው ንጽጽር፣
- ለ2012 በጀት ዓመት ለማሳካት የታቀዱ ዋና ዋና ውጤቶች፣
- በ2012 የሚከናወኑ ዋና ዋና የካፒታል ፕሮጀክቶች፣
- በ2012 ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሔ ዕርምጃዎች

3. **የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ መግለጫዎች**

የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ በጽሑፍ የሚገለጽበት ይሆናል።

4. **ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ያለው ትስስር /መ/ቤቱን የሚመለከት/**
ከአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰነድ ውስጥ ሴክተሩን የሚመለከት የተገለጹ ስትራቴጂዎች፣ የክፍለ ኢኮኖሚው ፕሮግራሞች እና ግቦች በአጭሩ የሚገለጽበት ነው።

5. የመ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች፣ የውጤት አመልካቾች እና ግቦች ማጠቃለያ **በሰንጠረዥ 1** መሰረት ይቀርባል።

6. **የ2012 የፕሮግራም በጀት ማቅረቢያ ቅጾች**

- የ2012 የበጀት ጥያቄ ማጠቃለያ በፕሮግራም ደረጃ በሰንጠረዥ 2 ይቀርባል::
- በዓመታዊ በጀት ማቅረቢያ በቅጽ -- አበማ1 መሠረት የ2012 ውጤቶች፣ የአፈጻጸም አመልካቾች/መለኪያዎች /Performance Indicators /Measures/ እና ግቦች /Targets/ ተለይተው ይቀመጣሉ::
- የ2012 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክቶች እና የመደበኛ ዋና ዋና ተግባራት በዝርዝር የወጪ መደቦች በዓመታዊ በጀት ማቅረቢያ -- በቅጽ አበማ2 በExcel ይቀርባል::
- ለካፒታል ፕሮጀክቶች ተያይዞ በሚገኘው በዓመታዊ በጀት ማቅረቢያ ቅጽ -- አበማ3 መሠረት ሙሉ በሙሉ ፕሮጀክቶች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ የፕሮጀክቶች መግለጫ (Project Profile) ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል:: የመ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በስራቸው ኮምፖኔንት ካላቸው በኮምፖኔንት ማቅረቢያ ቅጽ የኮምፖኖንቶች መግላጫ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት::

7. የዋና ዋና የመደበኛ ወጪዎች መግለጫ

   - ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ በመደበኛ ዋና ተግባራት ከፍተኛ ወጪ የያዙ ዋና ዋና የወጪ መደቦች መግለጫ ይቀርባል::

8. ደጋፊ ሰነዶች ወይም የፕሮጀክት የጥናት ሰነዶች አብረው ተያይዘው ይቀርባሉ::

9. የበጀት ዝግጅት ሰነዶች በወጥነት ለማዘጋጀት እንዲቻል፣

   - የሰነድ ጽሁፉ በWord Document ሆኖ በPower Geez Unicode መጻፍ ይገባዋል::
   - ቅጽ አበማ1፣ አበማ2፣ አበማ3 ሰንጠረዦች በExcel በPower Geez Unicode ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል::

ሠንጠረዥ 1

የዓላማዎች፣ ፕሮግራሞች/ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ውጤቶች፣ የውጤት መለኪያዎች እና ግቦች ማጠቃለያ

ዓላማ	ፕሮግራም	ውጤት	አመልካቾች	የ2012 ግቦች
ዓላማ 1	ፕሮግራም 1 /ከፕሮግራም መግለጫው ጋር/	ውጤት 1	የውጤት 1 መለኪያዎች	
		ውጤት 2	የውጤት 2 መለኪያዎች	
		ወዘተ		
ዓላማ 2	ፕሮግራም 2 /ከፕሮግራም መግለጫው ጋር/	ውጤት 1	የውጤት 1 መለኪያዎች	
		ውጤት 2	የውጤት 1 መለኪያዎች	
		ወዘተ		
ወዘተ				

ቅጽ አበማ 1- የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት የውጤቶች /Outputs/ ማጠቃለያ "ከላይ ወደ ታች" የሚዘጋጅ

የመ/ቤቱ መለያ ኮድ	የፕሮግራም መለያ ቁጥር			የፕሮግራም መግለጫ	የውጤት መለኪያ	በ2011 መጨረሻ የሚደረስበት የውጤቶች አፈጻጸም /baseline/	የ2012 ዕቅድ		የፋይናንስ ምንጭ					ማመሳከሪያ
	ፕሮግራም	ንዑስ ፕሮግራም	ውጤት				የፊዚካል ግብ	ወጪ	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤቱ ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	ከውጭ ብድር	ጠቅላላ ድምር	ወጪ - ጠቅላላ ድምር
1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13	14=10+11+12+13	15=9-14
000				የመ/ቤት ስም										
	1			*የፕሮግራም 1 ስም*										
				የፕሮግራም 1 ኃላፊ										
				ውጤት										
			1	የውጤት 1 ስም										
	2			*የፕሮግራም 2 ስም*										
				የፕሮግራም 2 ኃላፊ										
		2.1		የንዑስ ፕሮግራም 2.1 ስም										
				የንዑስ ፕሮግራም 2.1 ኃላፊ										
				ውጤቶች										
			1	የውጤት 1 ስም										
			2	የውጤት 2 ስም										
				ወዘተ										

ቅጽ አበ3 2 - የ2012 የፕሮግራም በጀት መጠየቂያ - በፕሮጀክት፣ በዋና ተግባርና በዝርዝር የወጪ መደቦች

የመ/ቤቱ መለያ ኮድ	የፕሮግራም መለያ ቁጥር			የፕሮግራም መግለጫ	የውጤቶች ዝርዝር				የፋይናንስ ምንጭ በዝርዝር የወጪ መደብ							ማመዛዘኛ
	ፕሮግራም	ንዑስ ፕሮግራም	ውጤት		የፕሮጀክት ወይም የተግባራት ስም	የፕሮጀክት ወይም የተግባራት መለያ ቁጥር /በበጀት አዋጁ መሰረት/	ዝርዝር የወጪ መደብ	ጠቅላለ ዓመታዊ ወጪ በዝርዝር ወጪ መደብ	ከመንግስት ግምጃ ቤት	ከመ/ቤቱ ገቢ	ከውጭ ዕርዳታ	የዕርዳታ ሰጪ ኮድ	ከውጭ ብድር	የብድር ኮድ	ጠቅላለ የፋይናንስ ምንጭ በዝርዝር ወጪ መደብ	ድምር=0
1	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13	14	15	16	17	18= (10(17)
000				የመ/ቤት ስም												
				የፕሮግራም 1 ስም												
	1			*የፕሮግራም 1 ኃላፊ*												
			1	የውጤት 1 ስም												
					የፕሮጀክት 1 ስም	የፕሮጀክት 1 ኮድ										
							6321									
							6324									
							6223									
							ወዘተ									
					የተግባር 1 ስም	የተግባር 1 ኮድ										
							6111									
							6313									
							ወዘተ									
	2			*የፕሮግራም 2 ስም*												
				የፕሮግራም 2 ኃላፊ												
		2.1		የንዑስ ፕሮግራም 2.1 ስም												
				የንዑስ ፕሮግራም 2.1 ኃላፊ												
			1	የውጤት 1 ስም												
					የፕሮጀክት 1 ስም	የፕሮጀክት 1 ኮድ										
							6321									
							6324									
							ወዘተ									
					የተግባር 1 ስም	የተግባር 1 ኮድ										
							6111									
							6313									
							ወዘተ									
				የውጤት 2 ስም												
					የተግባር 1 ስም	የተግባር 1 ኮድ										
							6111									
							6212									
							ወዘተ									

ቅጽ አበማ 2.1 ተጨማሪ የፋይናንስ መረጃ /ከአንድ በላይ ዕርዳታ ሰጪዎች ወይም አበዳሪዎች ካሉ የሚሞላበት/

የፕሮጀክት ስም	የአበዳሪ/ዕርዳታ ሰጪ ኮድ	የወጪ መደብ	የፋይናንስ ምንጭ			
			ከዕርዳታ		ከብድር	
			የገንዘብ መጠን	የዕርዳታ መለያ ኮድ	የገንዘብ መጠን	የብድር መለያ ኮድ

ቅጽ አበማ 3 - የ2012 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክቶች ዝርዝርና መግለጫ (Profile) ማቅረቢያ ቅጽ

በሚሊዮን ብር

የፕሮጀክቱ መለያ ኮድ /በበጀት አዋጁ መሰረት/	የፕሮግራሙ/ የፕሮጀክቱ ስም	የሚሰራበት ቦታ	የተጀመረበት ወርና ዓመት	የሚጠናቀቅበት ወርና ዓመት		የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ		የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ፅቅድ		እስከ 2011 ስድስት ወር መጨረሻ ድረስ የወጣ ወጪ /Expenditure To Date/	እስከ 2011 ስድስት ወር መጨረሻ የተሰራ የፊዚካል ሥራዎች የአፈጻጸም ደረጃ	ለ2012 በጀት ዓመት የሚሰራ የፊዚካል ፅቅድ	ለ2012 በጀት ዓመት የተጠየቀ በጀት	መግለጫ
				በመጀመሪያው ፅቅድ /Original Plan/	በተከለሰው ፅቅድ (ፅቅዱ ከተሻሻለ) /Revised Plan/	በመጀመሪያው ፅቅድ /Original Plan/	በተከለሰው ፅቅድ(ፅቅዱ ከተሻሻለ) /Revised Plan/	መለኪያ	የፊዚካል ሥራዎች ፅቅድ					
1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13	14	15
	ጠቅላላ ድምር													
	የፕሮግራም 1 ስም													
	የፕሮጀክት 1 ስም													
	ወዘተ													
	የፕሮግራም 2 ስም													
	የፕሮጀክት 1 ስም													
	ወዘተ													

ቅጽ አበማ 3.1 - የ2012 በጀት ዓመት የፕሮጀክት ኮምፖኔንቶች ዝርዝርና መግለጫ (Profile) ማቅረቢያ ቅጽ

በሚሊዮን ብር

የፕሮጀክቱ/ ኮምፖኔንቱ ስም	ኮምፖኔንቱ የሚጀመርበት ቦታ	ኮምፖኔንቱ የተጀመረበት ወርና ዓመት	ኮምፖኔንቱ የሚጠናቀቅበት ወርና ዓመት		የኮምፖኔንቱ ጠቅላላ ወጪ		የኮምፖኔንቱ ጠቅላላ ዕቅድ		እስከ 2011 ስድስት ወር ድረስ የወጣ ወጪ /Expenditure To Date/	እስከ 2011 ስድስት ወር መጨረሻ የተሰራ የፊዚካል ሥራዎች የአፈጻጸም ደረጃ	ለ2012 በጀት ዓመት የሚሰራ የፊዚካል ዕቅድ	ለ2012 በጀት ዓመት የተጠየቀ በጀት	መግለጫ
			በመጀመሪያው ዕቅድ /Original Plan/	በተከለሰው ዕቅድ (ዕቅዱ ከተሻሻለ) /Revised Plan/	በመጀመሪያው ዕቅድ /Original Plan/	በተከለሰው ዕቅድ(ዕቅዱ ከተሻሻለ) /Revised Plan/	መለኪያ	የፊዚካል ሥራዎች ዕቅድ					
1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13	15
የዋናው ፕሮጀክት ስም													
የኮምፖኔንት ስም													

የግንባታ ጣቢያ ቢሮ

110

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
Ministry of Finance

ቁጥር ገሚሣ/ሣ11/6/19
Ref No.
ቀን 30/5/2011
Date

ለ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡ <u>የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ጥያቄን ስለማቅረብ</u>

የፕሮግራም በጀት አሰራር የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ሀብትን ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ ዕቅድን ከበጀት፣ በጀትን ከውጤት ጋር እንዲያስተሳስር ታስቦ እየተተገበረ ይገኛል። በዚህም መሠረት የሶስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት ዘመን /2010-2012/ በ2010 በጀት ዓመት ተጀምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን የዚሁ የፕሮግራም በጀት ዘመን አካል የመጨረሻ ዓመት የሆነው የ2012 በጀት ዓመት ደግሞ በቀጣይ ይካሄዳል።

የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት መንግስት ራሱን እንደገና ካደራጀ በኃላ የሚዘጋጅ በመሆኑ መ/ቤቱ ነባር መ/ቤት ከሆነ በሶስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት ዘመን ለ2010-2012 የታቀደውንና በ2012 መጨረሻ የሚደረስበትን የዓላማዎች /Outcomes/ የግብ ስኬት መሠረት በማድረግ፤ አዲስ የተቋቋመ መ/ቤት ወይም የተዋሃዱ ወይም የተለያዩ ፕሮግራሞቹ ያላቸው መ/ቤቶች ከሆኑ ለአንድ ዓመት የሚሆን መነሻና መድረሻ ያላቸው ዓላማዎችና ፕሮግራሞች በመቅረጽ እንዲሁም የመ/ቤቱን የ100 ቀናት ዕቅድና የመንግስትን ትኩረት አቅጣጫ በመገምገም ማዘጋጀት ይገባል። ለተቀረጹትም ዓላማዎች መሳካት የሚያስፈልጉ ውጤቶች በመለየት በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ የሚደረስበትን የውጤቶች አፈጻጸም እንደመነሻ /Baseline/ በመውሰድ የ2012 ውጤቶች፣ የውጤቶች አመልካቾች እና ግቦች በማስቀመጥ በጀቱን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በተጨማሪም የተቀረጹ ውጤቶችን ለማሳካት በ2012 የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችና የመደበኛ ዋና ተግባራቶችን በመለየት የፕሮግራም በጀቱ በተደለደለው ጣሪያ መሠረት ተዘጋጅቶ መቅረብ ይገባዋል።

በዚሁ መሰረት የ2012 የፕሮግራም በጀት ጥያቄው ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚገኘው የፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ መሠረት ተዘጋጅቶ በHard Copy እና በSoft copy እስከ <u>መጋቢት 15 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ</u> እንዲቀርብ እያሳሰብን፣ ስለአቀራረቡ ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት ከተፈለገ የመ/ቤታችንን የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በማነጋገር መረዳት የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

<u>እንዲያውቁት፣</u>
- ለፊሲካል ፖሊሲና ፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ለኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ዴኤታ
- ለመንግስትና የግል አጋርነትና የልማት ድርጅቶች ባሳደራ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ገንዘብ ሚኒስቴር

RECEIVED
DATE 13 FEB 2017
OFFICE OF THE PRESIDENT

ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24 55 14 96 251-11-155 11 38
አስቸኳይ መልስ ሲፈልጉ የሞን ቁጥር ይጥቀሱ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa – Ethiopia

ለ2012 የተደለደለ የፕሮግራም በጀት ጣሪያ

በሺህ ብር

የወጪ ዓይነት/የገንዘብ ምንጭ	2012
ሀ. የመደበኛ ወጪ ድምር	1,619,940.00
ከመንግስት ግምጃ ቤት	1,538,023.00
ከመስሪያ ቤት ገቢ	81,917.00
ለ. የካፒታል ወጪ ድምር	600,000.00
ከመንግስት ግምጃ ቤት	600,000.00
ከመስሪያ ቤት ገቢ	-
ከውጭ እርዳታ	-
ከውጭ ብድር	-
ሐ. የፕሮግራም በጀት ጣሪያ ጠቅላላ ድምር	2,219,940.00
ከመንግስት ግምጃ ቤት	2,138,023.00
ከመስሪያ ቤት ገቢ	81,917.00
ከውጭ እርዳታ	-
ከውጭ ብድር	-